# Learning by Ear 2013

## "መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ "መዘዙን መቀበል"

## EPISODE 17: ምን እየሆንኩ ነው?

**AUTHOR: James Muhando**

**EDITORS: Friederike Müller, Maja Braun, Madelaine Meier**

**COPY EDITOR: Charlotte Collins**

**List of characters by scene:**

**<u>INTRO/OUTRO:</u> NARRATOR**

**<u>SCENE 1: ብሩክ IN HOSPITAL IN A BAD STATE</u>**

- **ወ/ሮ ሉሊት (F, 40)**
- **ብሩክ (M, 8)**
- **ቅዱስ (M, 8)**

**<u>SCENE 2: ንጉሴ AND HIS FATHER HAVE A TALK</u>**

- **አቶ ጃለታ (M, 45)**
- **ንጉሴ (M, 16)**

**<u>SCENE 3: አልማዝ AND በለጠ TALK AT BONGO ACADEMY</u>**

- **አልማዝ (F, 16)**
- **በለጠ (M, 16)**
- **እየሩስ (F, 15)**

**<u>SCENE 4: DR. ዶ/ር ሮቤል TALKS TO ወ/ሮ ሉሊት AND</u> ምህረት**

- **ዶ/ር ሮቤል (M, 50s)**
- **ወ/ሮ ሉሊት (F, 40)**

- ምህረት (F, 15)

## INTRO

## 1. NARRATOR:

ጤና ይስጥልን ዉድ የበማድመጥ መማር ታዳሚዎች፤  ይህ "መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ" በሚል ርዕስ  "መዘዙን መቀበል"የተሰኘዉ ሁለተኛው ዙር ድራማ ክፍል አስራ ሰባት ነዉ። ዛሬ ወደ ምናደምጠዉ አዲስ የድራማ ክፍል ከመግባታችን በፊት እስኪ ባለፈዉ ምን እንደተከሰተ እናስታወስ። የልውውጥ መርሃ-ግብር ተማሪዋ አልማዝ፤ ቦንጎ አካዳሚ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ደርሳ የሆነ ሰው እየፈለገች ነዉ።

## 2. EPISODE 15, LINES 65 – 69:

<u>አልማዝ</u>:  ኧም-ርዕሰ መምህርት ሰብለ የሆነ ነገር ልጠይቆ  እችላለሁ? እችላለሁ? (…)ዳንኤል ካኒያማን ያውቁት ይሆን?

<u>ርዕሰ መምህርት ሰብለ</u>  : ትክክል፡- አዎ፣ በርግጥ አዉቀዋለሁ፣ ዳንኤል ካባረርናቸው ተማሪዎች መካከል አንዱ ነው፡.

<u>አልማዝ</u>:  ምን? ለምን?

## 3. NARRATOR:

ምክንያቱ በእርግጥ  ትንሽ ምስጢራዊ  ነው፡፡ ዳንኤል አሁን ካረገዘችው የክፍል ጓደኛው ምህረት ጋር ተኝቷል፡፡ እርሷም እንዲሁ ከትምህርት ቤቱ ተባራለች ፡፡  የክፍል ጓደኛቸው ንጉሴም እጽ በመጠቀሙ ታግዷል፡፡ ሆኖም  በባለፈው ክፍል ድራማ  ምህረት ወደ ትምህርት ቤት መመለስ እንደምትችል የሚገልፅ ደብዳቤ ከርዕሠ-መምህርቷ አምጥቶ ሰጥቷታል፡፡ እናም ንጉሴ ይዞ የመጣው ዜና ግን ያ ብቻ አልነበረም፡፡

## 4. EPISODE 16, LINES 33 – 34:

<u>ንጉሴ</u>: ምህረት፣ ናፍቀሽኛል።.

<u>ምህረት:</u> ንጉሴ፣ እኔ…እያስቸገርከኝ ነው፤አላዉቅም

## 5. NARRATOR:

የምህረት ታናሽ ወንድም ብሩክ በሳንባ ነቀርሳ እየተሰቃየ ነው። ሐኪም ቤት የህክምና ክትትል እየተደረገለት ይገኛል። እናቱ እና መንታ ወንድሙ ቅዱስም ሊጠይቁት መጥተው ከአጠገቡ ይገኛሉ። እስቲ አሁን “ምን እየሆንኩ ነው?” በተሰኘው አስራ ሰባተኛው ክፍል ድራማ ሶስቱን እዛው ሐኪም ቤቱ ውስጥ አንድ ላይ ሆነው እናገኛቸው…

## <u>SCENE 1: ብሩክ IN HOSPITAL IN A BAD STATE</u>

**6. ATMO:** **HOSPITAL ATMO, INSIDE ብሩክ ROOM**

**7. ወ/ሮ ሉሊት :** ብሩክ፣ በደንብ አልበላህም! ይህን አጥሚት በተለይ ለአንተ ነዉ ያዘጋጀሁት ! **(whispers)** አውቃለሁ የሆስፒታል ምግብ እንጨት እንጨት ነው የሚለው።

**8. ብሩክ:** **(laughs weakly)** አልራበኝም ነበር እማ! ትንሽ ስላመመኝ ነዉ…

**9. ቅዱስ:** **(animated)** ብሩኬ፣ወንድሜ ፣ በደንብ የሚሻልህ መቼ ነው፣ ሲሻልህ ታንዲካ ፊልም የሚያሳየው ሰውዬ ጋር እወስድህ እና ባለቤቱን “አናኮንዳ” የሚባለውን ፊልም እንዲሳየን እጠይቀዋለሁ።

***KW BEGIN***

**10. ብሩክ:** **(still weak)** “አናኮንዳ” ምንድን ነው?

**11.** ቅዱስ: ትልቅ አባብ ነው! ተጠቅልሎ ተጠቅልሎ ተጠቅልሎ ሰዎችን ይውጥ እና መልሶ ይተፋቸዋል!

**12.** ብሩክ: ዋው፤ አሪፍ ይመስላል! አይተኸዋል?

**13.** ቅዱስ: አዎ ፡ ባለ ሱቁ ቦታውን በማጽዳት ስላገዝኩት በነጻ አስገባኝ። ስለ አንተም ነገርኩት እና ...

***KW END***

**14.** ወ/ሮ ሉሊት : ቅዱስ፣ ወንድምህን ማስቸገርህን ተው እና እነዚህን ነገሮች በመሰብሰብ አግዘኝ። ለጉብኝቱ የተሰጠን ጊዜ እያለቀ ነው። እናም የብሩክ ሀኪም ሊመረምረዉ አሁን ይመጣል።

**15. SFX: UTENSILS GATHERED**

**16.** ብሩክ: እማዬ፣ እያመመኝ ነው...እንደሚመስለኝ እኔ -- **(pukes)**

**17. SFX: SOUND OF SOMEONE PUKING**

**18.** ቅዱስ: **(disgusted and amused at the same time)**

ኢኢኢኢ፣ ብሩክ! ልክ እንደ አናኮንዳ!

**19.** ወ/ሮ ሉሊት : **(concerned)** ብሩኬ፣ ልጄ! ውይ በሞትኩት፣ የእኔ ምስኪን ልጅ!

**(to ቅዱስ)** ቅዱስ፣ ፍጠን ሂድና ዶክተር ሮቤልን ጥራቸው!

**20. SFX: RUNNING STEPS AS ቅዱስ LEAVES**

**21. SFX: DOOR BEING OPENED AND CLOSED**

**22. MUSICAL INTERLUDE**

**SCENE 2: ንጉሴ AND HIS FATHER TALK**

**23. SFX: CAR STARTING (HEARD FROM INSIDE)**

**24. ATMO: INSIDE MOVING VEHICLE**

**25.** አቶ ጃለታ: **(friendly)** እህሳ ንጉሴ እና ዋናውን ወደድከዉ?

**26.** ንጉሴ: በጣም አባዬ። መዋኘት ደስ ይለኛል።.

**27.** አቶ ጃለታ: እንዲህ በጣም ከወደድከው ታድያ በየጊዜው ለምን አትዋኝም?የዋናተኞቹ ቡድን አባል መሆንም ትችላለህ!

**28.** ንጉሴ: አላውቅም። አንዴም ትዝ ብሎኝ አያውቅም። ሁል ጊዜም የማስበው ስፖርት ላይ ጎበዝ አለመሆኔን ነው።

**29.** አቶ ጃለታ: አስብበት፣ እሺ?

**30.** ንጉሴ: እሺ።

**31. SILENCE**

**32.** ንጉሴ: አባዬ?

**33.** አቶ ጃለታ: አቤት ልጄ

**34.** ንጉሴ: ለምንድን ነው ሰው ሁሉ ሚጠላኝ?

**35.** አቶ ጃለታ: **(startled)** ምን? ለምን? **(realizes)** ስለዚያች ልጅ ነው?

**36.** ንጉሴ: **(annoyed)** አያይ፣ እርሱን እርሳው፡ በቃ!እኔ እራሴ ይሄን ጥያቄ ለምን እንደጠየቅሁ አላውቅም።

**37.** አቶ ጃለታ: እመንገዱ ዳር ላቁምና እንነጋገራለን።

**38. SFX: CAR COMES TO A HALT, ENGINE SWITCHED OFF**

**39.** አቶ ጃለታ: ስማኝ ልጄ! አሁን አሁን በጣም ጠጠር እንዳልኩብህ አውቃለሁ። ግን ያ ማለት እጠላሀለሁ ማለት አይደለም! ከዚህ በጣም ይለያል። ንጉሴ በአንተ እኮራብሀለሁ- እና በተለይ እጽ መውሰድ በማቆምህ ኮርቻለሁ።

***KW BEGIN***

**40.** ንጉሴ: **(hesitant)** ግን ለምንድነው ሴቶች የሚርቁኝ?

**41.** አቶ ጃለታ: እነዚህ ነገሮች አንተን መረበሽ የሚጀምሩበት እድሜ ላይ መሆንህን አውቃለሁ። ግን በምንም ተአምር በራስ መተማመንህን ማጣት የለብህም።

**42.** ንጉሴ: በራስ መተማመኔን አላጣሁትም። ግን ዝም ብዬ ነዉ የጠየቅኩህ።.

**43.** አቶ ጃለታ: አሃ ልክ ነው፡ አልኮል መጠጣትህ፣ ማሪዋና ማጨስህ እነዚህ ሁሉ በራስ መተማመን ማጣትህን ያሳዩ ነበር።

***KW END***

**44.** ንጉሴ: አንተን እና እናቴን አሳዝኜአችኋለሁ። ይቅርታ፣ እና ከትምህርት ቤት መባረሬን ስሰማ በእውነት አስደንግጦኛል…

**45.** አቶ ጃለታ: ርዕሰ መምህርት ሠብለ ሌላ እድል ሰጥታሀለች። ደግመህ እነዚያን አጾች እንደማትነካ ቃል ግባልኝ!

**46.** ንጉሴ: ቃል እገባለሁ!አሁን ማቆሜን ታውቃለህ።

**47.** አቶ ጃለታ: እኔም ቃል ልገባልህ እፈልጋለሁ። እነዚህን አጾች ደግመህ መውሰድ እስካልጀመርክ ድረስ ደግሜ እጄን በአንተ ላይ በቁጣ አላነሳብህም። እሺ? በል አሁን መዳፍህን ዘርጋና ቸብ ላርግልህ።

**48.** ንጉሴ: **(embarrassed)** ሾረ አባዬ እያሳፈርከኝ ነው።

**49.** አቶ ጃለታ: ና እንጂ ንጉሴ የእኔ ልጅ፣ የሚያየን ማንም የለም። የሽማግሌው ሰዉየህን እጅ ምታ !

**50.** አቶ ጃለታ/ንጉሴ: **CLAP (HIGH FIVE). THEY LAUGH.**

**51. SFX: CAR STARTS AGAIN AND DRIVES OFF**

**52. MUSICAL INTERLUDE**

**<u>SCENE 3: አልማዝ TALKS TO በለጠ IN THIE SCHOOL LIBRARY</u>**

**53. SFX: ATMO IN SCHOOL LIBRARY (SILENT, PAPERS BEING SHUFFLED, BOOK PAGES TURNED OVER)**

**54. SFX: PEN SCRIBBLING ON PAPER**

**55. በለጠ:** **(murmuring to himself)** ምን አይነት ጣጣ ነው! ይሄ የሚሰጠን የቤት ስራ የመጨረሻ ነው ያታከተኝ፡፡ እኔ ለእራሴ ከሰዓት በኋላ ቤተ-መጻህፍት ውስጥ መጎለት የመጨረሻ አይደለኝም!

**56. SFX: FOOTSTEPS - አልማዝ APPROACHES**

**57. አልማዝ:** ሠላም፣ በለጠ ነህ፣ አይደል?

**58. በለጠ:** **(not very friendly)** ሃይ አልማዝ.

**59. አልማዝ:** **(trying to start a conversation)** የእያንዳን ዱን ሰው ስም ማስታወስ ከባድ ነው! እኔ ግን የተቻለኝን ያህል እየሞከርኩ ነዉ…አጠገብህ ብቀመጥ ቅር ይልሀል?

**60. በለጠ:** ችግር የለዉም፣ ግን ትኩረቴን እዚህ ላይ ማድረግ አለብኝ፡፡ አለበለዚያ መቼም አልጨርሰውም!

**61. SFX: አልማዝ SITS DOWN ON WOODEN CHAIR**

**62. SFX: PEN SCRIBBLING ON PAPER AGAIN**

**63. አልማዝ:** በለጠ?

**64. በለጠ:** **(continues writing)** ህምምም?

**65. አልማዝ:** ከክፍላችን የታገዱት ዳንኤልን እና ሌሎችን ተማሪዎች ታውቃቸዋለህ አይደል?

**66. በለጠ:** ምምምህምም…

**67. አልማዝ:** ስለነሱ የሰማኸው ነገር አለ? ማለቴ ተመልሰዉ ይመጣሉ እንዴ?

**68. በለጠ:** አላውቅም።

**69. አልማዝ:** ሰው የሚያወራው ነገር እውነት ነው? ማለቴ …ዳንኤል እና ልጅቷ የተባረሩበት ምክንያት?

**70. በለጠ:** አልማዝ፣ እባክሽን አሁን ማንበብ አለብኝ።.

**71. SFX: PEN SCRIBBLING ON PAPER**

**72. አልማዝ:** **(sighs)** እሺ። እኔም ማንበብ ያለብኝ ይመስለኛል።

**73. እየሩስ:** **(whispering loudly from afar)** ሃይ፣ አልማዝ፣ ለምን እንደተባረሩ ትክክኛውን ምክንያት እኔ እነግርሻለሁ! ይህ ትምህርት ቤቱ ውስጥ የሚወራው አረፋ ወሬ ነው…

**74. አልማዝ:** **(interested)** እሺ፣ ሠላም እየሩስ

**75. በለጠ:** እሽሽሽ! አቦ ይሄ ቤተ-መጽሀፍት ነው!

**76. እየሩስ:** **(coming closer, whispering)** እሽ! አቦ ይህ ቤተ-መጽሀፍት ነው!...

**(fade out)**

**77. MUSICAL INTERLUDE**

## SCENE 4: ዶ/ር ሮቤል TALKS TO ወ/ሮ ሉሊት AND LATER TO ምህረት

78. **ATMO: HOSPITAL ATMO, INSIDE DR. ROBERT’S OFFICE**

79. **ወ/ሮ ሉሊት :** **(sniffles)**

80. **ዶ/ር ሮቤል:** ተቀመጭ፣ ወ/ሮ ሉሊት፡፡

81. **SFX: CHAIR SCRAPING**

82. **ወ/ሮ ሉሊት :** አመሰግናለሁ ዶ/ር ሮቤል፡፡ ስለ ልጄ ብሩክ ሃሳብ ገብቶኛል፡፡ መጀመሪያ ላይ ሲያስለው ቆየ፡፡ ከዚያም ሳንባ ነቀርሳ ያዘው እና ሆስፒታል ገባ፤ እዚህ ሆስፒታል እንኳ ገብቶ የሚሻለው አይመስልም! ለረጅም ጊዜ ተኝቷል!

83. **ዶ/ር ሮቤል:** **(serious tone)** የብሩክ እናት ልጅሽ ብሩክ እዚህ ሲመጣ አስጊ ሁኔታ ላይ ነበር፡፡ የምግብ እጥረት የነበረበት፣ ሰውነቱ የተዳቀቀ እና በሳንባ ነቀርሳ የተጎዳ ነበር፡፡ እናም በሽታው የታወቀለት ሰውነቱ ውስጥ ከተንሰራፋ በኋላ በመሆኑ ለማገገም ረጅም ጊዜ የፈጀበት ለእዚህ ነው፡፡ እንደዕድል ሆኖ ለህይወቱ የሚያሰጋው ነገር ባይኖርምያለበት ሁኔታ ትንሽ ማስጨነቁ አልቀረም፡፡

84. **ወ/ሮ ሉሊት :** **(starts to cry)** ወይ ልጄን!

85. **ዶ/ር ሮቤል:** ወ/ሮ ሉሊት እባክሽን አታልቅሺ፡፡ መድሀኒቱ ይጠቅመዋል፡፡ ግን ከባድ መድሀኒቶች ስለሆኑ ጠንካራ የጎን ችግሮችም ይኖራቸዋል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ማስመለስ እና ማቅለሽለሽ የሚሰማው ለእዚህ ነው፡፡ ግን ቶሎ ሊሻለው ይገባል፡፡.

**86. SFX: KNOCK ON THE DOOR**

**87.** ዶ/ር ሮቤል: አቤት?

**88. SFX: DOOR OPENS**

**89.** ምህረት: እንደምንዋላችሁ፣ ዶ/ር ሮቤል! እማ !

**90. SFX: DOOR CLOSED, STEPS ምህረት ENTER**

**91.** ወ/ሮ ሉሊት : ምህረት፣ የእኔ ልጅ!

**92.** ምህረት: እዚህ ከዶ/ር ሮቤል ጋር መሆንሽን የጤና ረዳቱ ነግሮኝ ነው። ምንድን ነዉ ነገሩ? ብሩክ ደህና ነው?

**93.** ወ/ሮ ሉሊት : ምህረቴ!

**94.** ዶ/ር ሮቤል: ወንድምሽ ይሻለዋል፣ ግን ምህረት አሁንም ቢሆን ሰውነቱ ገና በጣም አቅም እንዳነሰው ነው።.

**95. SFX: CHAIR SCRAPING AS ወ/ሮ ሉሊት GETS UP**

**96.** ወ/ሮ ሉሊት : በቃ ወደ ብሩኬ ልመለስ ።.

**97.** ምህረት: መጣሁ እኔም ከአንቺ ጋር ።.

**98.** ዶ/ር ሮቤል: ኧም…ምህረት፣ ለምን ትንሽ ቆይተሽ አትደርሺባትም? አንድ የማግርሽ ጉዳይ አለኝ።

**99.** ምህረት: (unsure) እሺ… በቃ ቶሎ እመጣለሁ እማዬ!

**100.** ወ/ሮ ሉሊት : ጥሩ የእኔ ልጅ።

**101. SFX: STEPS AS ወ/ሮ ሉሊት LEAVES**

**102. SFX: DOOR IS OPENED AND CLOSED**

**103.** ምህረት: ዶ/ር ሮቤል ሊነግሩኝ የሚፈልጉት ምንድን ነበር? ወንድሜ ብሩክን ለመርዳት ማንኛዉን ነገር አደርጋለሁ።

**104.** ዶ/ር ሮቤል: በርግጥ፣ ከአንቺ ጋር መነጋር የፈለግሁት ስለ እርግዝናሽ ነዉ፤

**105.** ምህረት **(embarrassed)** ዶ/ር፣ እኔ …እኔ …

**106.** ዶ/ር ሮቤል: **(calms her down)** ማፈር አያስፈልግም። እኔ ሀኪም ነኝ እንዳትረሺ፣ እና ይህ ደግሞ ስራዬ ነው። እና ታድያ ካረገዝሽ ምን ያህል ጊዜ ሆነሽ?

**107.** ምህረት: ህምም…ላስበው እስኪ። ምንአልባት ከአምስት ወራት ጥቂት ያልፍ ይሆን?

**108.** ዶ/ር ሮቤል: ከሆድሽ መጠን አኳያ ሊሆን ይችላል። የቅድመ ወሊድ ክትትል እያደረግሽ ነው?

**109.** ምህረት **(scared)** እንደ ወንድሜ ሆስፒታል ውስጥ መተኛት ያስፈልገኛል?

**110.** ዶ/ር ሮቤል: **(chuckles)** በፍጹም፣ በፍጹም። ቅድመ ወሊድ ህክምና ክትትል የሚያደርጉ ክሊኒኮች ነፍሰ ጡር ሴቶቸ ለመውለድ እንዲዘጋጁ አገልግሎት የሚሰጡ ናቸው። ክሊኒኮቹ የህጻኑን መጠን እና ጤንነት እየተከታተሉ የትምህርት እና የማማከር አገልግሎት ይሰጣሉ።

እርግዝናሽን ልትከታተዪ የምትችይባቸውንዝርዝር ቦታዎች በኋላ ልሰጥሽ እችላለሁ፡፡

***KW BEGIN***

**111.** ምህረት: ይህ ሁሉ ለምን ያስፈልገኛል? እናቴ ነፍሰ ጡር ስትሆን ክሊኒክ ሄዳ አታውቅም… እንደውም አንዲት ሴት እናት በምትሆንበት ጊዜ ምን ማድረግ እንደሚኖርባት እንደምታውቅ ነግራኛለች፡፡

**112.** ዶ/ር ሮቤል: በእርግጥ ማርገዝ እና መውለድ ሁለቱም የተፈጥሮ ሂደት መሆናቸው እውነት ነው፡፡ ግን አንዳንድ ጊዜ በጣም ተፈጥሯዊ ለሆኑ ነገሮች እንኳ መዘጋጀት ጥሩ ነው፡፡ የእናት እና ልጅ የህክምና ክትትል በወሊድ ጊዜ፣ ከወሊድ በፊት እና ከወሊድ በኋላም በጣም ጠቃሚ ነው፡፡ ልጁ በህይወት ለመቆየት የተሻለ እድል እንዲኖረው ይረዳል፡፡

**113.** ምህረት: ዋው፣ ያንን አላውቅም ነበር፡፡

***KW END***

**114.** ዶ/ር ሮቤል: ሌላው ደግሞ አንቺ በጣም ልጅ በመሆንሽ የአንቺ እና የእናትሽ እርግዝና ትንሽ ልዩነት እንዳለው አትዘንጊ፡፡.

**115.** ምህረት: አደገኛ ነው?

**116.** ዶ/ር ሮቤል: የግድ አስጊ ነው ማለት አይደለም፡፡ ግን አንዳንኤልድ ጊዜ የታዳጊ ልጆች እርግዝና ሰውነታቸው ገና ለእናትነት ሙሉ በሙሉ ስላልበቃ ውስብስብ ችግር ይኖረዋል፡፡

**117.** ምህረት: እያስፈራሩኝ ነው ዶክተር!

**118.** ዶ/ር ሮቤል: መፍራት አይኖርብሽም፣ ምህረት። ግን እራስሽንም ሆነ ልጁን በደንብ መንከባከብ አለብሽ። እና በርግጥ ሰውነትሽ ላይ ምን እየተከናወነ እንዳለ ማወቅ ጠቃሚ ነው።.

***KW BEGIN***

**119.** ምህረት: እባክዎ ንገሩኝ።

**120.** ዶ/ር ሮቤል: ጥሩ፣ የተወሰኑ ለውጦች ታያለሽ። በርግጥ ሆድሽ እያደገ እንደሆነ አሁንም አውቀሻል፣ እና ከተለመደው ይልቅ ሊርብሽ ይችላል። ይህ ደግሞ ማህጸንሽ ውስጥ እያደገ ያለው ህጻን ምግብ ስለሚፈልግ እሱን ለመመገብ አንቺ የበለጠ መመገብ ያስፈልግሻል። ልጅሽ ማደግ እና መጠንከሩን ስለሚቀጥል በእርግዝና ጊዜሽ የመጨረሻዎቹ ጥቂት ሳምንታት አካባቢ ይዞርና ጭንቅላቱን ወደ መውጫው ያዘቀዝቃል።

***KW END***

**121.** ምህረት: **(unsure**አንዳንድ ጊዜ ሆዴ ውስጥ የሆነ የሚኮረኩርነገር ይሰማኝና ያስቀኛል ሌላ ጊዜ ደግሞ  የሚረግጠኝ ይመስለኛል! ልጁ ነው?

**122.** ዶ/ር ሮቤል: **(laughs)** አዎ። ያ በጣም ጥሩ ምልክት ነው። ልጅሽ ማህጸንሽ ውስጥ እየተንቀሳቀሰ አንዳንድ ጊዜ የሚራገጥ ይመስላል።.

**123.** ምህረት: **(impressed)** አሀ…

**124.** ዶ/ር ሮቤል: እና ልጅሽ ጆሮዎች እንዳሉት እና ምን እየተካሄደ እንደሆነ እንደሚያዳምጥ ታውቂያለሽ?

**125. ምህረት:** እውነትዎን ነው?

**126. ዶ/ር ሮቤል:** አዎና። በእርግጥ እርሱን ማናገር መጀመር ትችያለሽ-ያ ከልጅሽ ጋር ያለሽን ትስስር ይጨምራል።.

**127. ምህረት:** ዋው፣ የሚደንቅ ነው!

**(thinks hard)** ግን ምን ልነግረው እችላለሁ?

***KW BEGIN***

**128. ዶ/ር ሮቤል:** **(laughing)** መልካም አንግዲህ ስለአዛልታሰቢበት በቂ ጊዜ ያስፈልግሻል። አሁን ወንድምሽ ብሩክን ሄደን እንየው?

**129. ምህረት:** **(remembers)** ብሩክ! እንዴት አረሳሁት!

**130. ዶ/ር ሮቤል:** አትጨነቂ። አሁን የምታስቢበት ብዙ ጉዳዮች አሉሽ። እና እንዳትረሺ፣ ሁሌም እኔን ወይም የስራ ባልደረቦቼን ምክር መጠየቅ ትችያለሽ.

***KW END***

## 131. <u>OUTRO – NARRATOR:</u>

**በእዚሁ የዕለቱ የበማድመጥ መማር መሰናዶአችን ያበቃል!"መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ በተሰኘዉ ድራማ ብዙ ክስተተች የሚከናወኑ ይመስላል። የድራማውን ያለፉትን ክፍሎች ማድመጥ ከፈለጋችሁ አልያም ድራማዉን በግል ማህደር መገልበጥ ከፈለጋችሁ በድረገጽ አድራሻችን <u>dw.de/lbe</u> ላይ ታገኙታላችሁ። በፌስቡክ አድራሻችን ዝግጅቶቻችን መከታተል ትችላላችሁ። በሚቀጥለዉ ክፍል ድራማ እስክንገናኝ እንሰናበታለን ጤና ይስጥልን።**